# ምዕራፍ ስባት

## ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊ ገጽታ



### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምንነትና አሰከፊ ገጽታዎች ደረጃውን በጠበቀ የኢ.ምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ጋር  የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን በተለያዩ ምሳሌዎች ውስጥ ከሥነምልክታዊ ውበታቸው ትጠቀማላችሁ፤
- ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን አስከፊነት በተመለከተ በግንዛቤ ላይ የተመሠረት አቋም ትይዛላችሁ፤
- የኢ.ምቋ አመልካች ግሶችን ባህሪያት በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ፣ ከምንባቡ ውስጥም የኢ.ምቋ አመልካች ግሶችን ትለያላችሁ፤
- ከሚሰጣችሁ ነጠላ ምልክቶች ድርብ ምልክቶችን በመመሠረት የምልክቶች አሠራር ብቃታችሁን ትገመግማላችሁ፤


## ቁልፍ ምልክቶች




ህገ-ወጥ




ሽፋን




የሰዎች-ዝውውር




ሚድያ




መጥለፍ




ተንኮል




ብዝበዛ




ማታለል



በዝባዥ




ዛቻ




ተበዳይ




በዳይ




መመልመል




መቆጣጠር




መካከለኛው ምስራቅ




እዳ




ሰነዶች




ማዋከብ



ሥነ-ልቦናዊ



ኮንትሮባንድ



ኢ-መደበኛ

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## የማነቃቂያ ተግባር

### እይታዊ ንባብ

የሚከተለውን ፎቶ በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።



## የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ‹‹ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር›› ሲባል ስትሰሙ ወይም ስታነቡ የምትገነዘቡት ምንድነው?
2. ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ የምታውቋቸው ኢትዮጵያዊያን ወደ ወጭ ሀገር የሄዱት በምን መንገድ ነው?
3. በሕጋዊ መንገድና በሕገወጥ መንገድ ከኢትዮጵያ መውጣት ልዩነቱ ምንድነው? ለምን?

መምህራችሁ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊ ገጽታ የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሐሰቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቀቄ ተመልከቱ።

## ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊ ገጽታ

የተ.መ.ድ. እ.ኤ.ኤ. በ2000ዓ.ም. ያወጣውና የፓሌርሞ ስምምነት በመባል የሚታወቀው ስምምነት በሰዎች መነገድ ወይም ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለብዝበዛ ዓላማ ሰዎችን (በተለይም ሴቶችና ሕፃናትን) በኃይል፣ በዛቻ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ በመጥለፍ ወይም በተበዳይ ላይ ኃላፊነት ላለው ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም በመስጠት መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ መደበቅ ወይም መቀበል ማለት እንደሆነ ይገልፃል። ሕፃናትን መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ መደበቅ ወይም መቀበል በራሱ በሰዎች መነገድ ተደርጎ ይወሰዳል። በሴቶችና በልጆች መነገድን የሚከለክለው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 597 እና 635 ላይም ይኸው ትርጉም ተቀምጧል። ከዚህ ትርጓሜ መረዳት እንደምንችለው፣ በሰዎች መነገድ በዋነኛነት ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል። እነዚህም፤ 1) በኃይል ወይም በማታለል መመልመል፣ (2) በአገር ውስጥ ወይም ወደ ሌላ አገር በህጋዊ ወይም በህገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር፣ እና (3) አዘዋዋሪዎች ተበዳዮችን የገንዘብ ጥቅም ማግኛ ማድረጋቸው (ብዝበዛ) ናቸው።

የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎች ለተለያዩ ጉዳቶች ይጋለጣሉ። ከሚኖሩበት አካባቢ ተነስተው ኢ-መደበኛ በሆኑ መንገዶችና በኮንትሮባንድ ንግድ መስመሮች የሚያደርጉት አደገኛ ጉዞ፣ በዝውውሩ ሂደት በአዘዋዋሪዎች እጅ የሚደርስባቸው ጥቃትና ብዝበዛ፣ በመዳረሻ አገራት የሚያጋጥማቸው አስከፊ የሥራ ሁኔታ ተደማምረው በተጠቂዎች ላይ ዘለቄታዊ የአካል፣ የአእምሮ እና ማህበራዊ ቀውስ ያሳድራሉ። ይባስ ብሎም በአዘዋዋሪዎች እጅና በተፈጥሮ አደጋ ሕይወታቸውን የሚያጡበት ሁኔታም ይፈጠራል።

ከግል ሕይወት አኳያ የሕገወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎች ወጣትነቻውን ከቤተሰቦቻቸውና ከማኅበረሰቡ ርቀው በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ ያሳልፋሉ። በመሆኑም የተሟላ ሰብእና ለመገንባት የሚችሉበት ጊዜ ይባክናል። ይህም ከሚደርስባቸው ብዝበዛና ጥቃት ጋር ተደማምሮ ለተለያዩ የስነልቦና ችግሮች ያጋልጣቸዋል። ከዚያም አልፎ የወንጀል ድርጊት ተሳታፊ እና ተጠቂ የመሆን እድላቸውን ያሰፋዋል።

ከማኅበራዊ ሕይወት አንፃር ደግሞ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎችን ከመደበኛው ማህበራዊ ምህዳራቸው በመነጠል ማኅበራዊ ሕይወታቸውን የማዛባት እንዲሁም ከማኅበራዊ ድጋፍ በማራቅ ይበልጥ ተጋላጭ እንዲሆኑ የማድረግ ውጤት አለው። በተለይም ተጠቂዎች የሚኖሩበት ሁኔታ ከለመዱት በእጅጉ የተለየ ሲሆንና መሰረታዊ እምነታቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ድርጊት እንዲፈፅሙ ወይም ባልተለመደ ማህበራዊ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ሲገደዱ (ለምሳሌ የቀጣሪዎቻቸውን እምነት እንዲከተሉ ሲገደዱ) ችግሩ የባሰ ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ማህበራዊ መገለልና ጫና በተጠቂዎች ላይ ዘላቂ ችግር በማድረስ ወደ ማኅበረሰባቸው ሲመለሱ በቀላሉ መቀላቀል እንዳይችሉና ገለልተኛ ሆነው እንዲቀጥሉ ያደርጋቸዋል።

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በተጠቂዎች ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ላይም የሚያሳድረው ጫና ቀላል አይደለም። ከመነሻው ሕገወጥ ደላሎች የሚጠይቁትና በማታለልም ሆነ በግድ የሚወስዱት ገንዘብ ከፍተኛ በመሆኑ የተጠቂዎች ቤተሰቦች ለከፍተኛ እዳ ይዳረጋሉ። ከዚያም አልፎ ብዙውን ጊዜ ደመወዛቸውን በጊዜውና ሳይቀናነስ የማግኘት እድል ስለማይኖራቸው በተመለሱ ጊዜ ለደረሰባቸው ስቃይ ማካካሻ ሊሆን የሚችል ገንዘብ አይኖራቸውም። አፍላ የወጣትነት ጊዜያቸውን ለአዘዋዋሪዎች ጥቅም ማሳለፋቸውም በዘላቂ ሕይወታቸው ሰርተው የማግኘት እድላቸውን ያጠበዋል።

ከሁሉም በላይ ጎልቶ የሚታየው ችግር ግን በተጠቂዎች ጤና ላይ የሚደርሰው ነው። የተለያዩ ጥናቶች እንዳሳዩት የአእምሮ መታወክ፣ አካላዊ ጉዳት እና ሞት በተጠቂዎች ላይ በተደጋጋሚ ይደርሳሉ። ተጠቂዎች እጃቸውና እግራቸው ተሰብሮ ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሞተው ሬሳቸው የሚመጣበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ ተከስቷል።

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ከግል ተበዳዮች አልፎ በሚኖሩበት ማኅበረሰብም ላይ ከፍተኛ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳት ያደርሳል። ችግሩ በአፋጣኝ ካልተፈታም ሙስና እና ንቅዘት እንዲስፋፉ ብሎም መንግስት የሕዝብን አመኔታ እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል።

*ጌታቸው ምትኩ. "በሰዎች መነገድ/ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምንድነው?". አብሲኒያለው ድህረ ገጽ፣ ለንባብ እንዲመች ተደርጎ የተዘጋጀ።*

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዟችሁ ታቅደው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በቃል መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢምቁ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቁ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቁ አንብቡ።

2. የምንባቡን መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢምቁ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣

ተገቢ መልሶችን በኢ.ምቋ አቅርቡ።

1. በተ.መ.ድ. ትርጉም መሠረት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ማለት ነው?
2. በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት በሰዎች መነገድ ምን ማለት ነው?
3. በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎች ላይ ዘለቄታዊ የአካል፣ የአእምሮ እና ማኅበራዊ ጠባሳ የሚፈጥሩት ምንድናቸው?
4. ከግል ሕይወት አኳያ ሕገወጥ ዝውውር በተጠቂዎቹ ላይ የሚያመጣው ችግር ምንድነው?
5. ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በተጠቂዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ የሚያሳድረው ጫና ምንድነው?
6. ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎች የሚደርስባቸውን የጤና ችግሮች ጥቀሱ
7. ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የሀገር ስጋት ሊሆን የሚችልባቸውን መንገዶች አስረዱ።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## አመልካች ግሶች

### አመልካች ግሶች

እነዚህ ግሶች ቋሚ አቅጣጫና እንቅስቃሴ የሌላቸውና በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዳላቸው አገባብ የሚለዋወጡ ግሶች ናቸው።

እነዚህ ግሶች አመልካች ግሶች የተባሉት በአጠቃቀም ጊዜ ምልክቶቹ መልእክቱ ወይም ንግግሩ ወደሚመለከተው ሰው ወይም አካል ስለሚያመለክቱ ነው። ማመልከት ሲባል ዝም ብለው ዐረፍተነገሩ ወደ ሚመለከተው አካል ይጠቁማሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን የምልክቱ አቅጣጫ መልእክቱ ወደ የሚመለከተው አካል ያሳያል ማለት ነው።

የስምና የተውላጠ ስም ተግባራትን ጨምረው ስለሚሰሩ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ግሶች ባሉበት ዐረፍተ ነገር ውስጥ የስም ወይም የተውላጠ ስም ምልክቶችን መጠቀም አያስፈልግም።እነዚህ ግሶች ምልክቱ እንደዚህ ነው ብሎ ማሳየት የሚቻል ቋሚ የሆነ አቅጣጫ የላቸውም። እንደ አገባባቸው አቅጣጫቸው

*መለዋወጥ ይኖርበታል።*

**ምሳሌዎች:**

*መበደር፣ መክፈል፣ መስጠት፣ መላክ፤ መምታት ፣ መመለስ፣ መርዳት፣*

*መገልበጥ፣ መጥራት፣ ወዘተ*

**አጠቃቀም፤**

**መበደር/ ማበደር**



*መበደር*



*ማበደር*

*ፎቶ: በኢ.መ.የ.ብ.ማ. የታተመው መዝገበምልክት*

**በማበደር ምልክት ላይ እንሚያሳየው የመበደር ምልክት ተመሳሳይ ሆኖ ምልክቱ የሚሠራው ወደ ተበደረው ሰው ነው። ተበዳሪው ሦስተኛ አካል ከሆነ ምልክቱ ወደ ጎን ይሠራል።**

**ምሳሌ፡ ሰጠ**

1. *መጽሐፍ አበበ ሰጠ (ወደ ውጭ)።* (ለአበበ መጽሐፍ ሰጠሁት።)
2. *መጽሐፍ አበበ ሰጠ (ወደ ውስጥ)።* (አበበ መጽሐፍ ሰጠኝ።)

በነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ መጽሐፍ ሰጪውና ተቀባዩ የሚታወቀው በግሱ (ሰጠ) አቅጣጫ ነው። የግሱ አቅጣጫ ከተናጋሪው ተነስቶ ወደ ውጭ (አበበ በአካባቢው ካለ ወደ እሱ) ስለሚሄድና ማን ለማን መጽሐፍ እንደሰጠ ስለሚያሳይ ሰጪው ተናጋሪው ከሆን እኔ ማለት አያስፈልገውም ። በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የግሱ አቅጣጫ ከውጭ ተነስቶ ወደ ተናጋሪው ይሄዳል። ይህም ተናጋሪው ተቀባይ መሆኑን ያሳይል።

**መታመም**

1. *ዓይን አመመ* ( ዓይኔን አሞኛል)
2. *እግር አመመ* (እግሬን አሞኛል)
3. *ራስ አመመ* (ራሴን አሞኛል)

በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የአመመ ምልክት የሚሠራው በታመመው አካል ላይ በመሆኑ፣ ዐረፍተ ነገሩ በአንድ ምልክት ብቻ ይገለጻል። ምልክቱ የታመመውን አካል ስለሚያመለክት ምልክቱ የሚያርፍበትን ቦታ መሠረት በማድረግ አድማጩ የታመመው አካል ምን እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

## መልመጃ አንድ

ከላይ ስለ አመልካች ግሶች የተሰጠውን ማብራሪያ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳዲስ ምሳሌዎች እያስደገፋችሁ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ

1. የኢምቋ አመልካች ግስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የኢምቋ አመልካች ግሶች ልዩ መለያ ምንድነው?
3. የኢምቋ አመልካች ግሶች ከገላጭና ከግልጽ ግሶች የሚለዩት በምንድነው?

## መልመጃ ሁለት

ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የሚከተሉት አመልካች ግሶች በተለያየ አገባብ ውስጥ ያላቸውን የተለያየ ምልክት በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳዩ።

1. መጥራት

2. መክፈል
3. መላክ
4. መመለስ
5. መርዳት

## መልመጃ ሦስት

ከምንባቡ ውስጥ አምስት አመልካች  ግሶችን ለይታችሁ አውጡና አጠቃቀማቸውን በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ አሳዩ።

ምሳሌ፡ ዝውውር

## ከነጠላ ምልክቶች ድርብ ምልክቶች መመሥረት

**በኢምቋ ሁለት ነጠላ ምልክቶችን በማጣመር ከሁለቱም ነጠላ ምልክቶች የተለየ ትርጉም ያለው አዲስ ምልክት መፍጠር ይቻላል። አዳዲሶቹ ምልክቶች አንድዬ ምልክቶች እንደሚባሉ ቀደም ባሉት ክፍሎች ተምራችኋል።**

**ምሳሌ፡**

1. ሕግ + መስበር = ሕገወጥ
2. መንግስት + ቤት = ቤተመንግስት
3. መናገር + ፓርላማ = አፈጉባኤ
4. ሁሉም + ሚኒስትር = ጠቅላይ ሚኒስትር
5. ማመስገን + የለም = ምስጋናቢስ

## መልመጃ

ከላይ በምሳሌዎቹ ውስጥ እንዳያችሁት ከነጠላ ምልክቶች የሚሰሩ አምስት አንድዬ ምልክቶችን ፈልጉና በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ አሳዩ።

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## የኢምቀ ናሙና ሰዋሰው

ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊ ገጽታ›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተስማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቋ አንብቡ።

1. *ኢምቋ፡ ሕግ መስበር ሰው መውሰድ መወሰድ ትርጉም ምን- የተለያየ ቦታ መቦጥቦጥ ዓላማ መሳካት መፈለግ ሰው ግድ ወይም ዋ-ዋ-ዋ- ወይም ማታለል ወይም ማፈን ወይም ጉቦ መሰጠት ምሳሌ አባት እናት ዘመድ መስጠት ከዛ ሰው መውሰድ ሌላ ቦታ ከዛ መጠቀም መጠቀም ራስ መጠቀም።*

   **አማርኛ፡** ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ለብዝበዛ ዓላማ ሰዎችን በኃይል፣ በዛቻ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ በመጥለፍ ወይም በተበዳይ ላይ ኃላፊነት ላለው ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም በመስጠት መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ መደበቅ ወይም መቀበል ማለት ነው።

2. *ኢምቋ፡ ይሄ ትርጉም ማሳየት ምን- ሰው ንግድ መጠቅለል ምን ሦስት ዋና ዋና*

   *ነገር።*

   **አማርኛ፡** ከዚህ ትርጓሜ መረዳት እንደምንችለው፣ በሰዎች መነገድ በዋነኛነት ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል።

3. *ኢምቋ፡ ሕግ መስበር መንገድ ሀገር ውስጥ ወይም ሌላ ሌላ ሀገር መውሰድ መውሰድ።*

   **አማርኛ፡** በሀገር ውስጥ ወይም ወደ ሌላ አገር በህጋዊ ወይም በሕገወጥ መንገድ ማዘዋወር፣

4. *ኢምቋ፡ ሕግ መስበር ሰው መውሰድ መውሰድ ሰው መምረጥ ጊዜ ከዛ አንደገና መውሰድ መውሰድ ጊዜ መቦጥቦጥ ጊዜ መቀጠል ሰው መቆጣጠር መጠቀም ዘዴ ልዩ ልዩ*

   **አማርኛ፡** ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ሰዎችን በመመልመል፣ በማዘዋወርና በመበዝበዝ ሂደት ተጠቂዎችን ለመቆጣጠር የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።

5. **ኢ.ምቃ፡** *ሕግ መስበር ሰው ልዩ ልዩ ቦታ መውሰድ መውሰድ ሰው መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ብዙ መብት መስበር ስቃይ መጋጠም።*

**አማርኛ፡ተጠቂዎች ከምልመላ ጀምሮ ባሉት ሂደቶች ሰብአዊ መብት ጥሰት ይፈጸምባቸዋል።**